# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

## ከ READ II ፕሮጀክት ጋር በመተባበር

## ለ“ትምህርት በቤቴ” መርሃ ግብር የተዘጋጀ

## የአምስተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት

ግንቦት 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማሳሰቢያ

ይኽን ለ"ትምህርት በቤቱ" መርሃ ግብር የሁለተኛ መንፈቀ ዓመት ማጠቃለያ ትምህርት አዘጋጅቶ ያቀረበላችሁ የሪድ II(READ II) ፕሮጀክት ከአሜሪካን ዓለም አቀፍ የልማት ተራድኦ ድርጅት (ዩ. ኤስ. ኤ. አይ. ዲ.) በሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ ነው። በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ይዘቶች በሙሉ ፕሮጀክቱን የሚያከናዉኑት ድርጅቶች ኃላፊነት ሲሆን የዩ. ኤስ. ኤ. አይ. ዲ.ን ወይም የአሜሪካን መንግስት አቋም የሚያንጸባረቁ ናቸው ማለት አይደለም።

## ስለሪድ **II (READ II)** ፕሮጀክት

የሪድ II (READ II) ፕሮጀክት አጠቃላይ ዓላማ እ.ኤ.አ በ2022 ትኩረት ሰጥቶ በሚሰራባቸዉ በአዲስ አበባ፣ አማራ፣ ኦሮሚያ፣ ሶማሊ፣ ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ እና በትግራይ ክልሎች 15 ሚሊዮን የሚሆኑ ህጻናት የንባብ ብቃታቸውን ማሳደግና በትምህርታቸው ውጤታማ ሆነው የተሻለ ሕይወት እንዲመሩ፤ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ እድገትም ወሳኝ ሚና እንዲጫወቱ ማገዝ ነው። ፕሮጀክቱን የሚተገብሩት ክርኤቲቭ አሶሼትስ ኢንተርናሽናል ከአጋሮቹ ኤዱኬሽን ዲቨሎፐመንት ሴንተር (EDC) ወርልድ ቪዥን ኢንተርናሽናል (WVI)፤ ኢንተርናሽናል ረስኪው ኮሚቴ (IRC) ቪያሞና ብሉትሪ ግሩፕ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከክልልና ከከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮዎች ጋር በመተባበር ነው።

- ❖ የምዕራፉ ዋና ርዕስ፡- የዱር እንስሳት በኢትዮጵያ

የምዕራፉ አላማዎች

ውድ ተማሪዎች ከዚህ የምዕራፍትምህርትማጠቃለያበኋላ፡-

- ✓ ውስብስብ ቃላትና ሀረጋትን በመነጠልና በማጣመር ታነባላችሁ።
- ✓ የተማራችኋቸውን አዳዲስ ቃላት በንግግርና በጽሁፍ ትጠቀማላችሁ።
- ✓ በማወዳደርደና በማነጻጸር ስልት ድርሰት ትጽፋላችሁ።
- ✓ በጽሁፋችሁ ውስጥ አንድ ነጥብን ወይም ይዘትን ትጠቀማላችሁ።
- ✓ የዓረፍተ ነገርን ባለቤት ትለያላችሁ ።

የምዕራፉ ይዘቶች

መነጠልና ማጣመር፣ አዳዲስ ቃላት በንግግር እና በጽሁፍ መጠቀም ፣ በማወዳደር እና በማነጻጸር ስልት ድርሰት መጻፍ፣ አንድ ነጥብን(ይዘትን) በጽሁፍ ውስጥ መጠቀም እና በዓረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤትን መለየት ይሆናል። ውድ ተማሪዎች በምዕራፍ 7 የቀረቡትን አላማዎች ለማሳካት እነዚህን ይዘቶች በሚገባ መረዳት ያሥፈልጋል።

- ❖ መነጠልና ማጣመር

በምዕራፍ ስድስት ስለመነጠልና ማጣመር ተምራችኋል። በመሆኑም በዚህ ምዕራፍ ገጽ 128 እና 145 ያሉትን የመነጠልእና የማጣመር ተግባራትን አንብቡ። በምታነቡበት ጊዜ ወላጆቻችሁ ወይም ሌላ የሚረዳችሁ ሰው በትክክል በመነጠል እና በማጣመር ማንበባችሁን እንዲያረጋግጡላችሁ አድርጉ። ጎበዞች! እነዚህን ውስብስብ ቃላት ከተለማማዳችሁ በኋላ ምንባብ ስታነቡ አትቸገሩም ማለት ነው።

ምሳሌ፡- አስተኔ-----ነጣጥሎ ማንበብ----አ-ስ-ተ-ኔ

ወደ-ሆድ- ኣቸው---- አጣምሮ ማንበብ ------ወደሆዳቸው

- ❖ አዳዲስ ቃላትን በንግግር እና በጽሁፍ መጠቀም

ተማሪዎች ባለፉት ምዕራፎች ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ እና ተቃራኒ ፍቺ መስጠትን በተመለከተ ተምራችኋል፤ አስታወሳችሁ? በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ በመስጠትና በአንቀጽ ውስጥ የተጓደሉ ቃላትን ማሟላት ትማራላችሁ። በመሆኑም በዚህ መልኩ አዳዲስ ቃላትን መጠቀም ትችላላችሁ ማለትነው። በገጽ 134 ላይ የተሰጠውን የማዛመድ እና ከምንባብ ውስጥ ቀለምን የሚገልጹ ቃላትን የመለየትና ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት የሚሉ መልመጃዎችን በመስራት መለማመድ ይኖርባችኋል ።

<u>ምሳሌ</u> ፡- <u>የቃላት ተመሳሳይ ፍች</u>

ገረጣ ---- ነጣ፣ አመዳማሆነ፣ ተጎሳቆለ...

አረፈ -----ሞተ

<u>የቃላት ተቃራኒ ፍች</u>

መልከ ጥፉ-------ውብ፣ ቆንጆ፣ ማራኪ....

የሰማይ ስባሪ----አጭር፣ ቀጭን፣ ደቃቃ

ተማሪዎች በምሳሌው መሰረት በገጽ 142 ላይ የሚገኙትንም በዚህ መሰረት አሟልታችሁ ጻፉ ።

❖ በ<u>ማወዳደር እና በማነጻጸር ስልት ድርሰት መጻፍ</u>

ወድ ተማሪዎች በምዕራፍ 5 ትምህርታችሁ በማወዳደር እና በማነጻጸር ስልት አንቀጽ እንደሚጻፍና የቢጋር ሰንጠረዥ እንዴት እንደሚዘጋጅ መማራችሁን አስታውሱ ። እንደምታስታውሱ ምእርግጠኛ ነኝ ። በማወዳደር እና በማነጻጸር ስልት ድርሰት ለመጻፍ ሲፈለግ በመጀመሪያ ሁለት ነገሮች ለውድድርና ለንጽጽር መቅረብ ይኖርባቸዋል። እነዚህን የቀረቡትን ሁለት ነገሮች በተመሳሳይነትና በልዩነት፣ በጥንካሬና በድክመት የሚነሱትን በመለየት ለርዕሰ ጉዳዩ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት በማድረግ ድርሰቱን አስፋፍተን መጻፍ እንችላለን።

<u>ለምሳሌ</u>፡-ባለፈው ትምህርታችሁ የእንስሳት እና የእጽዋትን ተመሳሳይነትና ልዩነት በተመለከት በማወዳደና በማነጻጸር ከቤት እንስሳትና ከዱር እንስሳት ለሰዎች ከመጥቀምና ከመጉዳት አንጻር የትኞቹ የተሸሉ እንደሆኑ ለአገር ኢኮኖሚም ከቱሪዝም አኳያ የሚያስገኙት ገቢ ወዘተ. በመሳሰሉት ሃሳቦች ላይ እጽዋት ለሰው ልጅ በምግብነት ፣ በመድሃኒትነት እንዲሁም ለቤት መስሪያነት በሚሰጡት ጥቅምም አያይዛችሁ አንደኛውን ርዕሰ ጉዳይ ጽፋችኋል። ለዚህም ተግባር የቢጋር ሰንጠረዥ ምሰርታችሁ ነበር። በዚህ መሰረት በተመሳሳይ በገጽ 134፣ 149 እና 150 ላይ የሚገኙትን ተግባራት በተሰጣችሁ የቢጋር ሰንጠረዥና ሀሳብ መነሻነት ተመሳሳዮችንና ልዩነቶች ንዘርዝሩ፣ የቢጋር ሰንጠረዥም አዘጋጁ ፣በመቀጠል በገጽ 142 ላይ ባዘጋጃችሁት የቢጋር ሰንጠረዥ መሰረት በማወዳደር እና በማነጻጸር ሁለት አንቀጽ ያለው ድርሰት ጻፉ። በገጽ 152 ላይ የሚገኘውን ስራ ደግሞ ከቤተሰቦቻችሁ ጋር ባዘጋጃችሁት በርዕሰ ጉዳይ መሰረት ተከራከሩበት ።

ውድ ተማሪዎች ይህ ስልት በጽሁፍ ላይ ብቻ የሚያተኩር ሳይሆን በንግግርም ወቅት መጠቀም እንችላለን ስለዚህ ገጽ 143 ላይ ንግግርን መሠረት አድርጎ የተዘጋጀውን ተግባር ስሩ ።

ወድ የተማሪ ወላጆች (አሳዳጊዎች)፡- ተማሪዎች እነዚህን ተግባራት ሲያከናው ኑአስፈላጊውን እገዛበ ማድረግ ልጆችን መርዳት ይኖርባችኋል ።

❖ <u>አንድ ነጥብ ወይም ይዘት (ነቁጥ)</u>

በምዕራፍ ስድስት ላይ የአንድ ነጥብ ወይም ይዘት (ነቁጥ) አገልግሎት እና አጠቃቀም ከነምሳሌው አይተናል ። ስለዚህ ያንኑ ማስታወሻ በማንቡበና በቀረቡት ምሳሌዎች መሠረት በገጽ 135 እና 151 ላይ ያሉትን ተግባራት በደብተራችሁ ላይ ስሩ ።

❖ <u>ከዓረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤትን መለየት</u>

ተማሪዎች በመጀመሪያ ዓረፍተ ነገር ምንነትን አስታውሱ። ዓርፍተ ነገር ምንድነ ው? ዓረፍተ ነገር ማለት አንድ ሙሉ ሃሳብን ወይም ስሜትን ሊገለጽ የሚችል የሐረጋት ስብስብ ነው።ዓረፍተ ነገር በዋናነት ባለቤት እና ማሰሪያ አንቀጽን በውሰጡ የያዘ ሲሆን አልፎ አልፎ እንደ ዓረፍተ ነገሩ አወቃቀር በውስጡ ሶስት ክፍሎች አሉት ። እነሱም ፡-

1. ባለቤት
2. ተሳቢ
3. ማሰሪያ አንቀጽ/ ግስ ናቸው ።

- የዓረፍተ ነገር ባለቤት፡- ማለት በዓረፍተ ነገር ውስጥ የድርጊቱ ፈጻሚ ወይ ምህላፊ ሆኖ የምናገኘው ነው ።

በሌላ አገላለጽ ባለቤት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ስማዊ ሀረግ ሲሆን ከግሱ ቀድሞ በዓረፍተ ነገር መጀመሪያ ላይ ይገባል። በአጭሩ በዓረፍተ ነገር ውስጥ ድርጊት ፈጻሚው ባለቤት ይባላል። የዓረፍተ ነገሩን ባለቤት ለማግኘት ማሰሪያ አንቀጹን ይዘን ማን የሚል ጥያቄ በመጠየቅ ምላሽ እናገኝበታለን።

<u>ምሳሌ</u> ፡- ለምለም መጻፍ ማንቡብ ትወዳለች ።

- መጽሐፍ ማንበብ የምትወደው ማንናት ? ለምለም ናት

ስለዚህ ‹‹ ለምለም›› የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት ናት ማለት ነው ።

- የዓረፍተ ነገር ተሳቢ፡- የዓረፍተ ነገር ተሳቢበ ስም ይወከላል። አብዛኛውን ጊዜ ድርጊቱ የተፈጸመው ድርጊቱን በፈጸመው አካል ነው። መገኛ ቦታውም በዓረፍተ ነገሩ መካከል ላይ ነው። ይህንን የዓረፍተ ነገር ተሳቢ ለማግኘት በተመሳሳይ የዓረፍተ ነገሩን ማሰሪያ አንቀጽ በመያዝ ምን ብለን ስንጠይቅ በቀላሉ ተሳቢውን ማግኘት እንደምንችል ማወቅ ያስፈልጋል።

ምሳሌ ፡- ነብሩ <u>ውሻውን</u> በላው። የተሰመረበት ቃል የዓረፍተ ነገሩ ተሳቢ ነው ።

- ነብሩ ምን በላ? ውሻውን በላ።

የሚለውን የዓረፍተ ነገሩን ተሳቢ ይጠቁመናል።

ተማሪዎች ስለ ተሳቢ ምንነት ለመረዳት በምዕራፍ ስድስት ላይ ስለ ሳቢና ሰለ ኢሳቢ ግሶች የተገለጸውን ሃሳብ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ ።

- ማሰሪያ አንቀጽ/ግስ፦ በዓረፍተ ነገር ውስጥ የተከናወነውን ድርጊት የሚያመለክትነው ።

ምሳሌ ፡- አለሙ ጫማ ገዛ ። የተሰመረበት ቃል ማሰሪያ አንቀጽ (ግስ) ነው።

ማስታዎሻ የወልና የተጸውኦ ስሞችም እንደ ባለቤት በመሆን ያገለግላሉ።

ምሳሌ ፡-ሀ. መሃመድ ፈረስ ጋለበ ።

ፈረስ የጋለበው ማን ነው ? መሃመድ ነው።(ባለቤት) ስለዚህ የዓረፍተ ነገሩ ባለቤት መሃመድ ነው ፤ የስሙ አይነት የተጸዉኦ ስም ነው።

ለ. ሰዎቹ ወደቤታቸው ተመለሱ ።

ወደ ቤታቸው የተመለሱት እነማን ናቸው? ሰዎቹ ናቸው ስለዚህ ሰዎቹ የዓርፍተ ነገሩ ባለቤት ናቸው ።

<<ሰዎቹ >> የሚለው ምን አይነት ስምነው ? የወል ስምነው ።

ውድ ተማሪዎች በዚህ ምሳሌ መሰረት በገጽ 138 ፣ 144 እና 153 ላይ የሚገኙትን ተግባራት በደብተራችሁ ላይ በመስራት ትክክል መሆናችሁን ለሚያግዟችሁ ሰዎች በማሳየት ትክክለኛነታችሁን አረጋግጡ ።

የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ሀ**.** ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች እንደየአጠያየቃቸው ትክክለኛ መልስ ስጡ።

**1.** በማነፃፀርና በማወዳደር ድርሰት ለመፃፍ ምን ያስፈልጋል?

2. አስራ አምስት ብር ከሰማንያ የሚለውን በቁጥር ፃፉ።

3. ረፍተ ነገር በውስጡ የሚይዛቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

4. ባለቤት ማለት ምን ማለት ነው?

5. የወል ስም ከተጸውኦ ስም በምን ይለያል?

ለ**.** ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን አማራጭ ምረጡ።

**1.**ከሚከተሉት አንዱ የወል ስም ነው?

ሀ)መሳይ ለ)ቶሎሳ

ሐ)አንበሳ መ)አባይ

2. በአንድ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተከናወነውን ድርጊት ዓይነት የሚያመለክት ቃል የቱ ነው?

ሀ)ተሳቢ　　　　　　　ለ)ግስ

ሐ)ቅፅል　　　　　　　መ)ባለቤት

3.በዓረፍተ ነገር ውስ ጥየድረጊቱ ፈፃሚ ወይም ኃላፊ ሆኖ የሚያገለግል ቃል ምን ይባላል?

ሀ)ቅጽል　　　　　　　ለ)ባለቤት

ሐ)ግስ　　　　　　　መ)ተሳቢ

4.የሚከተሉትን ቃላት የወልና የተጸውኦ በማለት ከለያችሁ በኋላ እንደ ባለቤት በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።

ሀ)አፍሪካ----

ለ)ድመት -----

ሐ)ሀይቅ------

መ)መልካሙ-----